15

710/2013

810/2300/42
10/5/2008

ለማስፈጸም አቅም ግንባታና የለውጥ ሥራ አመራር ቢሮ

ለሕዝብ ግንኙነትና ኮሚዩኒኬሽ ጽ/ቤት

ክ/ል/ኮ/ሚ/ር

ጉዳዩ፡- <u>የጸደቀ መመሪያ ስለመላክ፣</u>

በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ሥር በሚገኙ ሁሉም ቢሮዎች፣ ጽ/ቤቶች እና ተጠሪ ተቋማት ተፈጻሚ የሚሆነውን የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ዓርማ (Logo) መመሪያ ቁጥር 15/2005 ሆኖ ከህዳር 12 ቀን 2005 ዓ.ም. ጀምሮ የፀደቀ መሆኑ ይታወቃል።

ይሁን እንጂ ቀደም ሲል ተዘጋጅቶ ያልጸደቀው አርማ ለተለያዩ አግልግሎቶች (ለመኪና፣ለደብዳቤና ለተለያዩ ሕትመቶች ...) የዋለ በመሆኑ በጸደቀው አርማ (Logo) ሁሉም የሥራ ክፍል እንዲያስተካክል እያስታወቅን በዚሁ መሠረት የመመሪያውን አፈጻጸም እንድትከታተሉ የፀደቀው 1 ጥራዝ ሰነድ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ ተደርጐ የተላከ መሆኑን እንገልጻለን። የሠነዱ ግልባጭ የተመዘገበላችሁም መመሪያውን እንድታስፈጽሙት እናሳስባለን።

ከሰላምታ ጋር

መኩሪያ ኃይሌ ተ/ማርያም
ሚኒስትር

<u>ግልባጭ</u>

- ለክቡር ሚኒስትር ዴኤታ (የኮንስትራክሽን ዘርፍ)
- ለክቡር ሚኒስትር ዴኤታ (የከተማ ልማት ዘርፍ)
- ለሚኒስትር ጽ/ቤትና የሚኒካቢኔ ጉዳዮች ቢሮ
- ለማስፈጸም አቅም ግንባታና የለውጥ ሥራ አመራር ቢሮ
- ለከተማ መሬት ልማት ማኔጀመንት ቢሮ
- ለመሬትና መሬት ነክ ቋሚ ንብረት ምዝገባ ኤጅንሲ
- ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማትና ሬጉላቶሪ ቢሮ
- ለከተማ ኘላን፣ ጽዳትና ውበት ቢሮ
- ለከተሞች መልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ ቢሮ
- ለመኖሪያ ቤቶች ልማትና የመንግስት ሕንፃዎች ኮንስትራክሽን ቢሮ
- ለድጋፍ ሰጪ ማስተባበሪያ ቢሮ
- ለሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት
- ለተቀናጀ የመሬት መረጃ ኘሮጀክት ጽ/ቤት
- ለኦዲት መምሪያ
- ለሕግ መምሪያ

<u>ክ/ል/ኮ/ሚ/ር</u>
ከአንድ ጥራዝ አባሪ ጋር

710/2013

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር

15/2004

የዓርማ (Logo) አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 710/2013

ሀዳር 2005 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ዓርማ (Logo)

አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 710/2013

መግቢያ፡-

የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ያለብዙ ውጣ ውረድ በቀላልና በትንሽ ምልክት የተቋሙን ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ እሴቶች እንደዚሁም በማቋቋሚያ አዋጁ ተዘርዝረው የተሰጡትን ተግባራት የሚገልፅ ዓርማ (Logo) ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱና ይህንን ዓርማ (Logo) ለታለመለት ዒላማ ብቻ ሥራ ላይ የሚውልበትን ሥርዓት የሚገልፅ መመሪያ በማስፈለጉ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ይህን መመሪያ አዘጋጅቷል።

ክፍል አንድ
ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ፡-**

ይህ መመሪያ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ዓርማ (Logo) የአጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 710/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

በዚህ መመሪያ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር

1) "ዓርማ" ማለት አንድ ተቋም እንቅስቃሴውን (ሥራውን) በሚያከናውንባቸው ሥፍራዎች ላይ የሚውል ስም፣ ምልክት፣ የሥራውንም ዓይነት ለይቶ የሚያስረዳ ዓርማ/ምልክት ማለት ነው።

2) "ሰነድ" ማለት አርማው ሊታተምበት የሚችል ማንኛውም ወረቀት ወይም ሰሌዳ ነው።

3) "ተሸከርካሪ" ማለት በሚኒስቴር መ/ቤቱ በባለቤትነት የተመዘገበ ማንኛውም ተሸከርካሪ ነው።

The Federal Democratic Republic of Ethiopia • Ministry of Urban Development & Construction

3. <u>የዓርማው ዓላማ፡-</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በተቋቋመበት አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 25 ላይ በዝርዝር የተገለጹትን የተቋሙን ዓላማና ግብ እንደዚሁም በዝርዝ የተሰጡትን ሕጋዊ ተግባራት ሊወክል በሚችል ሕጋዊነት በሚኖረው ውክይና አጭር የምስል መገልገያ ተገልጋዩን በቀላሉ ግንዛቤ በማስጨበጥ ማሳወቅ ነው::

4. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ አርማ ተፈጻሚ የሚሆነው

1) በሚኒስቴር መ/ቤቱ፣በተጠሪ ተቋማት፣በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የግዛት ወሰን ክልል ውሰጥ በሚገኙ የፌዴራልና የክልል ከተሞች ላይ ነው::
2) ሚኒስቴር መ/ቤቱ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በሚፈጽማቸው የስምምነት ሰነዶች ላይ ነው::

<u>የዓርማው ስዕላዊ መግለጫ</u>

5. <u>የዓርማው (Logo) ቀለማትና ፊደላት ትርጉም</u>፡-

1) <u>አረንጓዴ ባለብዙ ወለል ሕንፃ (Green Multi story Building)</u>፦-

ሀ) ይህ የሚያመለክተው ከመኖሪያ ቤቱ ጫፍ ወደ ላይ ዕድገትን የሚያመለክቱ አቅጣጫ ጠቋሚዎች ሲሆኑ ይህም ሃገራችን በተግባር እያሳየች ያለውን ሕዝቡን ተጠቃሚ የሚያደርግ የተፋጠነ ልማትን ያመለክታል፤

ለ) በተጨማሪ በቀስቶቹ ላይ በሚፈጠረው ብርሃንና ጥላ አማካኝነት ሁለት አረንጓዴ ባለብዙ ወለል ዘመናዊ ሕንፃዎችን የሚያሳይ ሲሆን፤ አረንጓዴ ቀለሙ ማንኛውም ግንባታም ሆነ የምርት አቅርቦትና አገልግሎት ሂደት ለአካባቢ ጥበቃ ትኩረት የተሰጠ መሆኑን ያመለክታል።

2) <u>የመኖሪያ ሕንፃ</u>

ሀ) ይህ ምልክት የዜጎች መሰረታዊ ፍላጎት የሆነውን ለዜጎች በርካታ የስራ ዕድል መፍጠር ያስቻለውን እና ለቁጠባና ቋሚ ንብረት ማፍራት መሰረት የሆነውን የመኖሪያ ቤት ግንባታን የሚያመላክት ነው።

ለ) የመስኮት ምልክቱ የመኖሪያ ቤትን ለመግለፅ የተቀመጠ ሲሆን ሃገራዊ ራዕያችንንም አሻግረን የምናይበትን መስመር የሚያመላክት ነው።

ሐ) በስሩ ያሉ ደረጃዎች ፈጣንና ተከታታይ ልማትን ማምጣት እጅግ ፈታኝ ኃላፊነት መሆኑን ያሳያል።

መ) ከመኖሪያ ቤቱ ስር ያለው ሰማያዊ ድጋፍ ለመኖሪያ ቤት ልማት የተሰጠውን ትኩረትና ድጋፍ ያመለክታል።

3) <u>ሽበል (Tower Crane)</u>፡-

ይህ የሚያመለክተው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው በሁሉም የሃገራችን ከተሞች የሚካሄድ ማንኛውም ግንባታ በቁሳቁስም ሆነ የግንባታ ማሽነሪዎች የታገዘ እና

አጠቃቀሙን ጠንቅቆ ባወቀ እና በሰለጠነ የሰው ሃይል የተደራጀ እና አለም አቀፍ የጥራት ደረጃውን ጠብቆ እንደሚካሄድ የሚያሳይ ምልክት ነው።

4) ሰማያዊ ክብ ምልክቶች፡-

ሀ) እነኚህ ሰማያዊ ምልክቶች የሚወክሉት በአንድ በኩል የልማትና የለውጥ ሰራዊትን ሲሆን አቀማመጣቸው ሰውን ከላይ ወደ ታች (Top View) በምንመለከትበት ጊዜ ይህንን አይነት እይታ ሲኖረው ይህ ምልክት በአለም አቀፍ ደረጃ የሰዎችን ሕብረት ይገልፃል።

ለ) የእነዚህ ክብ ምልክቶች መያያዝ የልማትና የለውጥ ሰራዊት በተሳሰረ ጠንካራ የስራ ትጋት የተገነባ መሆኑን ያመለክታል።

ሐ) ሰማያዊ ክብ ምልክቶች ከዋና ከተማችን ከአዲስ አበባ ጀምሮ በክልሎች በፍጥነት በማደግ ላይ ያሉ ከተሞችን ያመላክታል።

መ) የሰማያዊ ምልክቶቹን ያስተሳሰረው የሞተር ጥርስ በከተሞች የሚታየው ልማት በኢንዱስትሪ ልማት የሚታገዘ መሆኑን ከማመልከቱ በተጨማሪ የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማትን የሚያመለክት ሲሆን ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት የከተማ ልማት አንቀሳቃሽ ሞተር መሆናቸውን ያሳያል።

6. የቅጠል ምልክት (Green Leaf) ፡-

1) ይህ ምልክት አረንጓዴ ቅጠል የልምላሜ እና የልማት ተምሳሌት በመሆኑ በከተሞቻችን እየታየ ያለውን የአረንጓዴ ልማት ጥረት እና የምዕተ ዓመቱ የልማት ዕቅድ የሆነውን የአካባቢ ጥበቃ ትኩረትን ያመለክታል፤

2) የቅጠሉ ሁለተኛው ግማሽ የኳስ ስቶን ንጣፍ ሲሆን ይህም ሁለተኛውን የልማት አማራጭ ያመላክታል።

7. ሰማያዊ (9) ከዋክብት (Stars)፡-

1) እነኚህ የሚወክሉት ዘጠኙን ክልሎች ሲሆን በመጀመሪያ ከላይኛው ኮከብ (የፌደራል መንግስት) በሚወጣው ብርሃን መተሳሰራቸው እንዲሁም በፌደራል ደረጃ ያለው

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከክልሎች ጋር ያለውን ጥብቅ የልማት ቁርኝት፣ ድጋፍና ክትትል የሚገልጽ ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ ከዋክብቱ በአረንጓዴ ቀለም መተላለፊያቸው የገጠርና የከተማ ትስስርን ሲወክል በሌላ በኩል እርስ በእርስ ያላቸውን ሕብረት እና ትብብር ብሎም አንድነታቸውን ያመላክታል፣

2) ከዋክብቶቹ በመጠን እኩል መሆናቸው ብሔር ብሔረሰቦች ያላቸውን በእኩልነት ላይ የተመሰረተ አንድነትና የመልማት ዕድል ያመለክታል።

8. <u>ኪ.ል.ኮ.ሚ</u>፡-

ይህ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱን ስያሜ የአማርኛ ምህፃረ ቃል ነው።

9. <u>MUDCo.</u>:-

ይህ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱን ስያሜ በእንግሊዘኛ ምህፃረ ቃል የሚገልጽ ነው።

10. <u>የዓርማው (Logo) መጠንና አጠቃቀም</u>፡-

ይህ የመ/ቤቱ ዓርማ የስፋቱ መጠን በሚታተምበት የሰነድና ሌሎች ንብረቶች መጠን የሚወሰን ሆኖ ክብሔራዊ አርማ ጋር የሚውለበለብ ሲሆን የአርማውን ቁመትና ወርድ በተመለከተ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 13 የተደነገገው ተፈጻሚ ይሆናል።

11. <u>የዓርማ ምንነት</u>፡-

የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ዓርማ (Logo) (ከዚህ በኋላ «ዓርማው» እየተባለ የሚጠራ) የሚኒስቴር መ/ቤቱ እና እንደሁኔታው እርሱ ለሚቆጣጠራቸው ሕጋዊ ተቋማት ስለሚኖራቸው ተግባራት፣ ዓላማና ግብ ሥራ ላይ እንዲውሉና ተገልጋዮችም በአጭርና ቀላል የምልክት መለያነት እንዲያውሉት የተዘጋጀ ዓርማ (Logo) ነው።

12. <u>የዓርማው ቀለማትና ቅርጽ</u>፡-

የዓርማው መደብ ነጭ ክብ ሆኖ በላዩ የሚከተሉት ዝርዝሮች (ምልክቶች) ይኖሩታል፡-

1) አረንጓዴ ባለብዙ ወለል ሕንፃ (Green Multi story Building)፤

2) የመኖሪያ ቤት (Housing)፤

3) ታወር ክሬን (Tower Crane)፤

4) ሰማያዊ ክብ ምልክቶች፤

5) የአረንጓዴ ቅጠል ምልክት (Green Leaf)፤

6) የመ/ቤቱ ሙሉ ስም በአማርኛና በእንግሊዝኛ፤

7) እንዲሁም በምህፃረ-ቃል(Abbreviation) በአማርኛና በእንግሊዝኛ (ከ.ል.ኮ.ሚ (MUDCo.) ይኖሩታል።

ክፍል ሁለት

የዓርማው አጠቃቀም

13. <u>ሌሎች ልዩ ልዩ አጠቃቀሞች፡-</u>

የሚስቴር መ/ቤቱን ዓርማ በተንቀሳቃሽ ተሸከርካሪዎች ላይ፣ በብሮሸሮች፣ በእስቲከሮች፣ በመ/ቤቱ ፖስታዎች፣ በደብዳቤ መጻጻፊያ ሰነዶች፣ መ/ቤቱን በሚወክል ከብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ ጎን በሚውለበለብ ላይነን ጨርቅ ላይ እና በቢሮ ጠረጴዛዎች ወይም በስብሰባ አዳራሾች ውስጥ መጠቀም የሚቻል ሲሆን ከብሔራዊ የሰንደቅ አላማ ጋር ቢሰቀልበት ጊዜ አርማው ከብሔራዊ ሰንደቅ አላማ በስተግራ በኩል ይሆናል።መጠኑም በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሰንደቅ አላማ አዋጅ ቁጥር 654/2001 አንቀጽ 10 መሠረት የተደነገገው መጠን ሆኖ የሚኒስቴር መ/ቤቱን ተግባርና ኃላፊነት የሚያንፀባርቀው አርማ (ሴንተሩን ጠብቆ) መሃል ላይ ይቀመጣል

14. <u>በዓርማው አጠቃቀም የተከለከሉ ሁኔታዎች፡-</u>

ማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት ከዚህ በታች የተመለከቱትን ተግባራት መፈፀም ክልክል ነው፡-

1) ሚኒስቴር መ/ቤቱ አጽድቆ የተቀበለውን ዓርማ ዓላማና ግብ እንደዚሁም መነሻ ምክንያትና ሀሳብ ለሚባረር መግለጫ መጠቀም፤
2) ዓርማውን በጨርቅ በራስጌ ጽሑፍ (heading letter)፣ ወይም በብሩሸሮችና እስቲከሮች ላይ ሥራ ላይ እንዲውል ሲደረግ ገልብጦ ወይም ዘቅዝቆ መጠቀም፤
3) የዓርማውን አቀራረጽ፣ ይዘትና ምስል አዛንፎ በመቅረፅ (በማዛባት) ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ዕውቅናና ፈቃድ ሳይሰጥ ሥራ ላይ ማዋል፤
4) በዓርማው ላይ ማንኛውንም ዓይነት ጽሑፍ መጻፍ፣ ሌሎች ምልክቶች ወይም ስዕሎችን ለጥፎ መገልገል።

15. <u>ቅጣት</u>፡-

1) ማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት የሚኒስቴር መ/ቤቱን ተልዕኮ ለማሰናከል ወይም ሌላ ከባድ ወንጀል ለመፈፀም ዓርማውን በሽፋንነት የተገለገለ ሆኖ ሲገኝ አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ መሠረት ተጠያቂ የሆናል

2) ድርጊቱን የፈፀመው የመ/ቤቱ ሠራተኛ ሲሆን በፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 አንቀጽ 67 እና በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 77/1994 መሠረት እንደ ጥፋቱ መጠን የዲስፕሊን ቅጣት ይወሰንበታል፤

16. <u>መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ</u>፡-

ይህ መመሪያ ከህዳር 12 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

መኩሪያ ኃይሌ

የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር

ሚኒስትር